# JIH ፖሊሲ፣ በተማሪ ላይ የሚደረግ ምርመራ፣ ፍተሻ እና መታሰር

ዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ለሠራተኞች እና ለተማሪዎች ደሕንነት እና ጤና  አስተማማኝ ጥበቃ የሚያደርግ ለመማር ማስተማሩ ሂደት አመቺ የሆነ ድባብ በትምህርት ቤቶች ውስጥ እንዲኖር እና ይህም ተጠብቆ እንዲዘልቅ ማድረግ ይፈልጋል። ይህን ግብ ለመምታት፣ ለተማሪዎች ወይም ለሠራተኞች ደሕንነት እና ጤና አስጊ የሆነ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ማናቸውም ዓይነት ንብረትን የያዘ ግለሰብን ወይም አስጊ ነገሩን የያዘውን ንብረት የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ለመፈተሽ ሊገደዱ ይችላሉ። የአደንዛዥ ዕፅ ወይም ሌሎች ወንጀሎች ምርመራ እና ፍተሻ በሚደረግበት ጊዜ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ከአካባቢው ሕግ አስፈጻሚ አካላት ጋር የትምህርት ቤቱን ንብረት እና በትምህርት ቤቱ ውስጥ ፍተሻ እንዲደረግ መተባበር አለበት።

**በትምህርት ቤት ሠራተኞች የሚደረግ ፍተሻ፥**

ፍተሻ ቢደረግ ተማሪው የትምህርት ቤቱን ፖሊሲ ወይም ሕግ ስለመጣሱ ማስረጃ ሊያዝ እንደሚችል እምነት ያደረበት የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ወይም የት/ቤት ባለስልጣን ፍተሻ እንዲደረግ ሊያዝ ይችላል። ፍተሻ መደረግ እንዳለበት በቂ ምክንያት ካለ፣ የት/ቤት ሠራተኞች ተማሪውን ወይም የተማሪውን የግል ንብረት በትምህርት ቤት ወይም በትምህርት ቤት በተዘጋጀ ዝግጅት በመሳተፍ ባለበት ቦታ ላይ ፍተሻ ሊያደርጉበት እና በዚህ ፖሊሲ በተቀመጠው መሰረት የሚገኝ ማናቸውንም ሕገወጥ፣ ያልተፈቀደ ወይም ኮንትሮባንድ ዕቃ በቁጥጥር ሥር ማድረግ ይችላሉ።

ማናቸውም በት/ቤቱ ሠራተኞች የሚደረግ ፍተሻ እንደ ተማሪው ዕድሜ እና ጾታ እንዲሁም የተጠረጠረው ነገር ምንነት ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ፣ የተማሪውን ክብረ ገበና የጠበቀ፣ ከሚያስፈልገው በላይ በግል ሕይወቱ ጠልቆ ያልገባ መሆን አለበት።

**የትምህርት ቤት ንብረት ላይ የሚደረግ ፍተሻ፥**

ማናቸውም በዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ያሉ ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ዕቃ ማስቀመጫ ተቆላፊ ሳጥኖች፣ ዴስኮች እና ሌሎች ዕቃ ማስቀመጫዎች ንብረትነታቸው የዲስትሪክቱ ሲሆን፣ በየትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህራን ሥር ይተዳደራሉ። በተጨማሪ፣ እያንዳንዱ የግል ሳጥን ቁልፍ ለተማሪው በት/ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም ወኪሉ የሚሰጠው ሲሆን የቁልፉ ዋና ግልባጭ ዝርዝር ወይም መቆለፊያ መሳሪያ በት/ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም ወኪሉ እጅ ይቀመጣል። በትምህርት ቤቱ ለተማሪው የተሰጠ ንብረት በዚህ ፖሊሲ መሰረት በማናቸውም ጊዜ ምርመራ ሊደረግበት፣ ሊጸዳ፣ ሊጠገን እና ሊፈተሽ ይችላል።

ተማሪዎች በአስተዳዳሩ ተቀባይነት ባለው መልኩ ለሚረከቡዋቸው የግል ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖች ወይም ሌሎች ዕቃ ማስቀመጫዎች ደሕንነቱን የመጠበቅ ኃላፊነቱን ይወስዳሉ። ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ በተሰጣቸው ዴስክ፣ የግል ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን ወይም ሌሎች ዕቃ ማስቀመጫዎች ላይ ለሚገኝ ነገር ኃላፊነቱን ይወስዳሉ።

ርዕሰ መምህሩ ወይም ወኪሉ በተፈለገ ጊዜ ፍተሻ መደረግ እንዳለበት ጠቋሚ ሁኔታ ሲኖር ፍተሻው ምክንያት ያለው ይሁን አይሁን፣ ውጤት ያስገኝ አያስገኝ የት/ቤቱን የተጠረጠረ ዴስክ፣ የግል ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን ወይም ሌሎች ዕቃ ማስቀመጫዎችን መፈተሽ/ማስፈተሽ ይችላል። ፍተሻ የሚደረግባቸው ነገሮች የሴት የእጅ ቦርሳዎች፣ የወንድ የኪስ ቦርሳ፣ የደብተር መያዣ ሻንጣ እና የልብስ ኪሶች ሊሆኑ ይችላሉ። የትምህርት ቤት ባለስልጣናት በተጨማሪ ለፍተሻው በቂ አጠራጣሪ ምክንያት ካላቸው በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ የቆመ መኪናን መፈተሽ ይችላሉ። በማናቸውም ሁኔታው በሚፈቅድበት ሁኔታ ሁሉ ፍተሻ ሲደረግ በእማኝነት የሚያይ ሌላ ሰው መገኘት አለበት።

**በተማሪ አካል ላይ የሚደረጉ ፍተሻዎች፥**

ፍተሻ ቢደረግ ተማሪው ኮንትሮባንድ ዕቃ እንደያዘ ወይም ሕግ፣ የስኩል ዲስትሪክቱን ፖሊሲዎች ወይም የትምህርት ቤቱን ደንቦች ስለመጣሱ ማስረጃ ሊያዝ እንደሚችል እምነት ያደረበት የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ወይም ወኪሉ የተማሪውን አካል ሊፈተሽ ይችላል።

አካላዊ ፍተሻዎች በተማሪው ኪስ፣ ተማሪው ሊይዛቸው በሚችሉ እንደ የሴት ቦርሳ ወይም ሳምሶናይት እና/ወይም ከልብስ ጋር "ልጥፍ" ብለው በተሰፉ ኪሶች መገደብ አለበት። ለምሳሌ፣ ሸሚዝ፣ ካናቴራ፣ ወይም ሙታንታ እንዲወልቅ የሚያስገድድ ልብስ የማውለቅ ፍተሻ በዲስትሪክት ሠራተኞች ሊደረግ አይችልም።

በተማሪ ላይ የሚደረጉ አካላዊ ፍተሻዎች ሲከናወኑ በተቻለ መጠን የተማሪውን የግል ሕይወት ላለመንካትና ክብረ ገበናውን ለመጠበቅ እንዲቻል በግል ከሌሎች ተማሪዎች ተለይቶ መደረግ አለበት። በተቻለ መጠን ፍተሻ ሲደረግ ፍተሻ ከሚደረግበት ተማሪ ጾታ ጋር ተመሳሳይ ጾታ ያለው ሠራተኛ በሌላ ተመሳሳይ ጾታ ባለው እማኝ ፊት ይደረጋል።

**ንብረቶችን በቁጥጥር ሥር ማዋል፥**

ሕግ ወይም የዲስትሪክት ፖሊሲ ወይም የትምህርት ቤት ደንብ ስለመጣሱ ወይም ተይዞ በመገኘቱ የአካል ጉዳት ሊያስከትል የሚችል በትምህርት ቤት ባለስልጣናት ፍተሻ ሲደረግ የሚያዝ ማናቸውም ነገር በቁጥጥር ሥር ይውላል።

**በትምህርት ቤት ባለስልጣናት የሚደረግ ምርመራ፥**

ተማሪዎች በዲስትሪክት ሠራተኞች በማናቸውም ጊዜ ምርመራ ሊደረግባቸው ይችላል። ወላጁ ወይም ወላጇ ወይም አሳዳጊው/ዋ በአካል ሳይገኙ ወይም እንዲገኙ ወላጅየው፣ አሳዳጊው ወይም ተማሪው ለትምህርት ቤቱ በሰጡት መገኛ አድራሻ ለማግኘት በቂ ሙከራ እስካልተደረገ ድረስ አንድ በቀጥታ ከትምህርት ቤት ሊያስባርረው የሚችል ወንጀል እንደፈጸመ/ች የታመነበት/ባት ተማሪ ስለፈጸመው/ችው ወንጀል በጽሑፍ ቃሉን/ቃሏን እንዲሰጥ/እንድትሰጥ አይደረግም።

**መግለጫዎች፥**

"ምክንያታዊ ጥርጣሬ" ማለት ከአንድ ታማኝ ጠቋሚ ወይም የትምህርት ቤቱ ባለስልጣን ካለው ልምድ በመነሳት በግሉ ባደረገው ትዝብት አንድን የተወሰነ ግለሰብ፣ ቦታ ወይም ነገር ፍተሻ ቢደረግበት፣ የቦርዱ ፖሊሲ፣ የትምህርት ቤቱ ደንብ ወይም የስቴት ወይም የፌደራል ሕጎች ስለመጣሳቸው አሳማኝ መረጃ ሊገኝ እንደሚችል ሲያምን ማለት ነው።

"ኮንትሮባንድ ዕቃዎች" አደንዛዥ ዕፆችን፣ አልኮል መጠጦችን፣ ሽጉጦችን፣ ቢላዋዎችን ወይም ሌሎች የጦር መሣሪያዎችን ወይም እሳት ሊያስነሳ የሚችል መሳሪያን ጨምሮ በነዚህ ነገሮች ያልተገደበ ማናቸውም ንጥረ ነገር ወይም ቁስን ያጠቃልላል።

**ሕግ ለማስከበር የሚደረግ ፍተሻ እና በቁጥጥር ሥር ማዋል፥**

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም ወኪሉ በሕግ አስከባሪ መኮንን በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ፍተሻ እንዲደረግ ሊጠይቅ ይችላል። ሕግ አስከባሪ መኮንኖች ፍተሻ ሲያደርጉ፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ሕግ አስከባሪ መኮንኑ በቀጥታ ትዕዛዝ ካልሰጠ በቀር እገዛ ከማድረግ ወይም በፍተሻው ላይ በቀጥታ ከመሳተፍ መቆጠብ አለባቸው።

ሕግ አስከባሪ ሠራተኞች አንድን ተማሪ ወይም የተማሪ ንብረት ለመፈተሽ እንዲፈቀድላቸው የትምህርት ቤቱን ባለስልጣናት በሚጠይቁበት ጊዜ፣ የሚከተሉት ሁኔታዎች ስለመኖራቸው ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ካላሳወቁ በቀር፣ የትምህርት ቤቱ ባለስልጣናት ፍተሻው ከመደረጉ በፊት ፖሊስ ተገቢውን የፍርድ ቤት የመፈተሻ ትዕዛዝ እንዲያቀርብ መጠየቅ አለባቸው፥

1. ያለ ምንም ማስፈራራት ተማሪው ስምምነቱን የገለጸ እንደሆነ።

2. የፍርድ ቤት ፍለጋ ትዕዛዝ እስከሚመጣ ድረስ በሚጠፋው ጊዜ ፍተሻው ሊደረግ የታሰበበት ዒላማ ሊጠፋ የሚችል ከሆነ፣ ወይም

3. ፍለጋው ከእስር ጋር የተገናኘ እና በግለሰቡ እና በአካባቢው ተፈጻሚነት ካለው።

**በፖሊስ የሚደረግ ምርመራ፥**

አንድን በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም በት/ቤት በተዘጋጀ ዝግጅት ላይ በመሳተፍ ላይ ያለን ሕግ ወይም የቦርድ ፖሊሲ ጥሷል ተብሎ የተጠረጠረ ተማሪን ሕግ አስከባሪ መኮንኖች ምርመራ ለማድረግ ፈቃድ ሲጠይቁ፣ የት/ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም ወኪሉ በምርመራው ወቅት በአካል መገኘት አለባቸው። ተማሪው ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች ከሆነ፣ በስቴት ሕግ ቃሉ እንደሚተረጎምበት አስተረጓጎም የሚወሰን ሆኖ ራሱን እንዲችል የተፈቀደለት ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ካልሆነ በቀር በምርመራው ወቅት ወላጅ/አሳዳጊ መገኘት አለበት።

ምርመራው በሚደረግበት ጊዜ ሌሎች በተማሪው ላይ ትኩረት እንዳያደርጉ ምርመራውን በተቻለ መጠን ምስጢራዊ በማድረግ በትምህርት ቤቱ አሰራር ላይ ጉልህ መስተጓጎል እንዳይፈጠር ተገቢው ጥረት መደረግ አለበት።

***ወህኒ/መታሰር፥***

ወህኒ ቤት መውረድ እና/ወይም እስር በፖሊስ በኩል ሲፈጸሙ፣ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ሁሉም አስፈላጊ የሕግ የአካሄድ መስፈርቶች መሟላታቸውን መጠየቅ አለበት። ርዕሰ መምህሩ ለፖሊስ መኮንኑ ተማሪውን ካስረከበ በኋላ ስለሁኔታው ለተማሪው ወላጆች ያሳውቃል። የፖሊስ መኮንኑ ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ወደ ጊዜያዊ ማረፊያ ቤት ሊወሰድ የቻለበትን ምክንያት ያሳውቃል። የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህርም ስለተወሰደው እርምጃ፣ ምክንያቱንም ለወላጆች ያሳውቃል፣ እንዲሁም ይህን መረጃ በማስታወቂያ መመዝገቢያ መዝገብ ውስጥ ያሰፍራል። የማስታወቂያው አንድ ቅጂ በትምህርት ቤቱ ፋይል ውስጥ የሚቀመጥ ሲሆን ሌላ አንድ ቅጂ ደግሞ ለወላጆች ይላካል።

እንዲጣጣም ተደርጎ የተዘጋጀው ኤፕሪል 15፣ 1971
እንደገና የተሻሻለው ፌብሩዋሪ 1፣ 1983
እንደገና የተሻሻለው ፌብሩዋሪ 15, 2001
እንደገና የተሻሻለው ኦክቶበር 21, 2004

ሕጋዊ ዋቢዎች.: C.R.S. 19-2-201 et seq.
C.R.S. 19-2-511 at seq.
C.R.S. 22-32-109.1(2)(a)(VIII) (policy required as part of safe schools plan)
C.R.S. 22-33-106.3

ተዛማጅ ማጣቀሻ፥ JK, Student Discipline, and subcodes
JLIB, Student Dismissal Precautions